# የጠ/ሚ የሲአል ጉብኝት !

ጠ/ሚንስትራችንና ከአሜሪካውና ከእንግሊዙ አቻቸው ጋር በመሆን ከስጥናዔል በተደረገላቸው ግብዣ መሰረት በሲኦል ኦፊሰላዊ ጉብኝት ለማድረግ ይሄዳሉ፡፡

እንደደረሱም ሳጥናዔል በክብር ተቀብሎ በጋለ ብረት ምጣድ ላይ ያሳርፋቸዋል; ከዚያም እያዟዟረ ገሃነብ እሳቱን ሲያስጎበኛው; ሁሉም በድንጋጤ ተውጠው; ሲሞቱ ወደ ገሃነብ እሳት እንዳይገቡ በመፍራት ከአሁን በኋላ ክፉ ነገር እንደማይሰሩ ስልጣንም ለቀው በጾም በጸሎት እንደሚኖሩ ወዲያውኑ ላራሳቸው በራሳቸው ቃል ይገቡና; ከመቸኮላቸው ብዛት ገና ወደ ምድር ሳይመጡ እዛው ሆነው ስልክ በመደወል ስልጣን ለቀናል ለማለት ይጣደፋሉ።

ሳጥናዔልም ስልክ ያቀርብላቸውና ሂሳብ ግን እንደሚከፍሉ ይነግራቸዋል;

ሁሉም ተስማምተው ስልክ ማጮህ ይጀምራሉ; መጀመሪያ; ቡሽ ደወለና 5 ደቂቃ አናግሮ ሂሳብ ስንት ነው ብሎ ሲጠይቅ በደቂቃ 1 ሚሊዮን በጠቅላላው 5 ሚሊዮን ይባልና ይከፍላል።

የእንግሊዙም 5 ደቂቃ አናግሮ 5 ሚሊዮን ፓውንድ ይከፍላል፡፤ የኛው ጉድ ደግሞ 30 ደቂቃ ሙሉ ይቀድና ሂሳብ ሲል 30 ብር ይለዋል። በዚህ ግዜ ቡሽና ብሌር በሳጥናዔል አድሎ ይናደዱና ለምንድነው እኛን ለ 5 ደቂቃ 5 ሚሊዮን አስከፍለህ እሱን ለ30 ደቂቃ 30 ብር ብቻ የምታስከፍለው ብለው ይጠይቃሉ፡- ሳጥናዔልም ፡-

የእናተ ኢንተርናሽናል ኮል ነው የሱ ግን ሎካል ኮል ስለሆነ ነው፡፤ ብሎዋቸው እርፍ....!